ግንቦት 7
የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

Ginbot 7
Movement for Justice, Freedom and Democracy

# በአገራችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ ግድ ይላል፤ ለዚህም ተግተን እንሰራለን!

ህዳር 6 2002

መንግሥቴን ለመገልበጥ ሙከራ አድርጋችኋል በሚል በወያኔ ተከሰው እየተሰቃዩ የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰው ያለው ሰቆቃ በቃላት መግለጽ እማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ንቅናቄዓችን ከዚህ በፊትም በዚህ ጉዳይ ላይ ባወጣው መግለጫ በደርግ ጊዜ እንኳን ያልነበሩ የሰቆቃ ዓይነቶች – ለምሳሌ በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሞቅ መሳሪያ ጭንቅላት ማጋል – በወያኔ መዳፍ ውስጥ ባሉ የፓለቲካ እስረኞች ላይ ተፈፃሚ እየሆነ እንደሆነ ገልፀን ነበር:: ሰቆቃ መፈጸም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተገወዘ አረመኔዓዊ ድርጊት ቢሆንም በወያኔ እስር ቤቶች ግን በየጊዜው እየባሰበት የሚሄድ የወያኔ መርማሪዎችና ሰላዮች የእለት ተእለት ተግባር አካል ነው።

ወያኔ ዜጎችን ለማጥቃት ሲፈልግ ወንጀሉንም ማስረጃውንም እራሱ እየፈበረከ ባለበት ሁኔታ በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን እስረኞችን ማሰቃየት ለምን ፈለገ? መልሱ አንድ ብቻ ነው – ክፋት!!! በጥላቻ በተለይም በዘረኛ አመለካከት የደነደነ ሥር የሰደደ ክፋት!!!!

ወያኔ ለዘመናት ባካበተው የዘር ጥላቻ እየተነዳ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን እየፈጸመ ይገኛል። ወያኔ ሊታረምና ሊሻሻል የማይችል የክፋት ኃይል ነው። መወገድ ይኖርበታል ብለን የምናምነውም ለዚህ ነው::

ትናንት ህዳር 4 ቀን 2002 ዓም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት የተፈፀመው ኩነት በትምህርታዊነቱ የሚጠቀስ ነው። ይህ ችሎት ከህግ ጋር ፈጽሞ ዝምድና የሌለው የወያኔ የክፋት ውሳኔዎችን በህግ ቋንቋ እየቀባባ የሚያቀርብ መድረክ መሆኑ ይታወቃል። ጀግኖቻችን ከወያኔ ፍርድ ቤቶች በተለይም ከዚህ ችሎት ፍትህ እንደማይገኝ አላጡትም። ህዳር 4 ቀን ባደረጉት የተባበረ ጥረት ግን የተደበቀው የእስረኞች ሰቆቃ አደባባይ እንዲወጣ ለማድረግ ችለዋል።

ሁሉም ታሳሪዎች በጋራ በመቆምም አፋቸውን ሊዘጓቸው ያሰቡትን ዳኞችን በመንፈስ ብርታት አሸንፈው የደረሰባቸው ሰቆቃ ለመላው ዓለም የማስረዳት እድል አግኝተዋል። ብ/ጄኔራል አሳምነው ጽጌ የዳኞቹን ክልከላ ተጋፍተው የደረሰባቸውን አውሬዓዊ ድብደባ በማብራራት የግራ ዓይናቸው መጥፋቱን እና የአንገት ሃብላቸው ከአንገታቸው ቆዳ ጋር አብሮ መወሰዱን አብራሩ። ከዚህም በተጨማሪ ደብዳቢዎቻቸው ዘራቸውን እያንቋንሸሹ እንደቀጠቀጧቸው በመግለጽ የድብደባው ዋነኛ ምክንያት ምን እንደነበር እንድናውቅ አደረጉን። በተመሳሳይ ሁኔታም ሻለቃ መኮንን ወርቁም የደረሰባቸው ድብደባ ዘረዘሩ፤ በአካሎቻቸው ላይ የደረሰውንም ጉዳት አሳዩ። ብ/ ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ ብ/ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ እና ሻለቃ መኮንን ወርቁ በሰቆቃ የተጎዱ አካሎቻቸውን እያሳዩ በቁጭት ያደረጓቸው ንግግሮች፤ የሌሎች ጓዶቻቸው ቁርጠኝነት እና በአዳራሹ የታደመው ሕዝብ ስሜት ተደማምረው አሻንጉሊቶቹ ዳኞች መናገር አስቻላቸውና የእስር ቤቱን አለቃ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቁት። የእስር ቤቱም አለቃ "እኔም ከእናንተ ጋር አሁን ገና መስማቴ ነው" ሲል ተሳለቀ። አሻንጉሊቶቹ ዳኞች ከዚህ በላይ መጠየቅ አልቻሉም – መመሪያ መቀበል አለባቸውና ነገሩን በቀጠሮ አሳደሩት። በታጋዮቻችን ላይ እየደረሰ ባለው ሰቆቃ እጅግ የተቆጨን ቢሆንም በመንፈስ ጥንካሬዓቸው ኮርተናል።

ከእስር ቤት ውጭም በታሳሪዎች ዘመዶች ላይ ተከታታይ ወከባና እንግልት እየተፈፀመባቸው እንደሆነ የሚደርሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ወያኔ በአንድ በኩል ከተቀናቃኞቹ ጋር ስምምነት እየፈጠረ ያለ የሚያስመስል ማጭበርበሪያዎችን እየከወነ በሌላ በኩል ደግሞ ዘርን መሰረት ያደረገውን ጥቃት በከፋ ሁኔታ ቀጥሎበታል።

በታሳሪዎቻችን ብርታት የወያኔ እስር ቤቶች የሰቆቃ መፈጸሚያዎች የመሆናቸው ሃቅ ይፋ ሆኗል። እስካሁን እያዩ እንዳላዩ ዝምታን ሲመርጡ የነበሩ ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች፤ ዓለም ዓቀፍ ተቋማትና መንግሥታት ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ዘር ላይ ያተኮረ ሰቆቃ በወያኔ እስርቤቶች ውስጥም ውጭም እየተፈጸመ መሆኑ የማሳወቅ ዘመቻዎችን እንዲያፋፍሙ እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ትኩረቱንና ኃይሉን ይህንን የከፋት ምንጭ የሆነውን ወያኔን በማስወገድ በምትኩ ፍትህ የሰፈነባት ነፃይቱን ኢትዮጵያን በመገንባት ትግል ላይ እንዲያውል ጥሪ እናደርጋለን። በአገራችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ ግድ ይላል፤ ለዚህም ቀና ሌሊት ተግተን እንሰራለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**